# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 214 ሰኔ 14 2004 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ዘርፍ የሚያደርገውን አፈና አጥብቆ ይቃወማል። መለስ ካልተወገደ በስተቀር እንዲህ ዓይነቱ ለማመን የሚቸግሩ ህገ-ወጥ እርጃዎች ይኖራሉ። ለንቅናቄዓችን መፍትሄው ግልጽ ነው። ይህም መለስ ና እና አገዛዙን ማስወገድ ነው። እኛ ለዚህ ተነስተናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኛ ጋር ነውና ነፃነታችንን እንቀዳጃለን።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ባለሥልጣኖች ከህዝብ የዘረፉትንና በሙስና ያከማቹትን ገንዘብ ከአገር በማሸሽ ተግባር ላይ መጠመዳቸው ታወቀ

በኑሮ ውድነትና በፍትህ እጦት ምክንያት ውስጥ ለውስጥ እየተቀጣጠለ የመጣው ህዝባዊ ተቃውሞ በፈጠረው ስጋት መለስ ዜናዊ በየደረጃው ያስቀመጣቸው ባለሥልጣኖች ከህዝብ የዘረፉትንና በሙስና ያጠራቀሙትን ገንዘብ ወደ ውጪ ሚንዛሪ እየቀየሩ ከአገር ማሸሽ ላይ መሆናቸውን የግንቦት 7 ታማኝ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ።

ያለምንም ችሎታና ልምድ የፖለቲካ ታማኝነታቸው ብቻ እየታየ በተለያየ የሥልጣን እርከኖች ተሹመው አገዛዙን በማገልገል ላይ ያሉ ከታች ከወረዳ እስከ ሚንስትርነት የተሰገሰጉ ሁሉ በአገኙት አጋጣሚ የዘረፉትን የአገር ሃብትና የህዝብ ገንዘብ ማሸሽ የጀመሩት በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ብሶትና ቁጣ በድንገት ሊፈነዳና ሥር ዓቱን ሊንድ ይችላል በሚል ስጋት እንደሆነ ለማወቅ ተችሎአል።

ፈረንጅ አገር በሚኖሩ የቅርብ ዘመዶቻቸው አለያም ጓደኞቻቸው አማካይነት ገንዘባቸውን ወደ ውጪ ምንዛሪ በገፍ እየቀየሩ ማሸሽ የተያያዙት እነዚህ የአገዛዙ ባለሟሎች ልጆቻቸውንና የቅርብ ቤተሰቦቻቸውንም ጭምር ከአገር ለማስወጣት ቪዛ የሚያገኙበትን መንገድ ሁሉ እየሞከሩ እንደሆነም ምንጮች ያደረሱን መረጃ ያመለክታል።

ባለሥልጣኖቹ የተሰማሩበት የሃብት ዘረፋና ሙስና ለማስቆም አንዳንድ የህወሃት ባለሥልጣናት የተለያየ ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ አዘል መመሪያዎችን በቅደም ተከተል ከላይ ወደታች ለማስተላለፍ ቢሞክሩም ሰሚ እንዳላገኙ የገለጹት እነዚህ ምንጮች ህወሃቶች ከሴላ ብሄረሰብ ታማኝ ሎሌዎችን ለማፍራት ሲሉ ሆን ብለው ከፍተው የለቀቁትን ዘረፋና ሙስና ለመቆጣጠር አሁን የፈለጉበት ዋናው ምክንያት የህብረተሰቡን ቁጣ ለማቀዝቀዝ ይችሉ እንደሆን ዕድላቸውን ለመሞከር እንደሆነ ገልጸዋል።

ወያኔ በቅርቡ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ውስጥ ያስቀመጣቸውን ታማኝ አገልጋዮቹን በሙስናና ሃብት ዘረፋ ምክንያት ለመወንጀል ግምገማ አካሂዶ በነበረበት ወቅት አንዳንድ የጋምቤላ ክልል ባለሥልጣኖችና የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት ሽፈራው ሺጉጤ ዘረፋውን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ከገቡ አገሮች ተርታ ተመደበች

ፎሬን ፖሊሲ መጋዚን ባወጣው የፌልድ ስቴትስ /failed states/ ኢንዴክስ ኢትዮጵያን ከአለም አገሮች በ17ኛ ደረጃ በማስቀመጥ፣ ለአደጋ የተጋለጠች አገር ሲል ፈርጇታል። ለኢትዮጵያ ሀልውና አስጊ ሆነው ከቀረቡ ችግሮች መካከል የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ የስደተኞች መብዛት፣ የህዝብ ብሶቶች መጨመር፣ ዜጎች አገራቸውን ጥለው መሰደድ፣ የፖለቲካ መሪዎች ልዩነት እና የጸጥታ ሀይሎች ጣልቃ ገብነት የሚሉት ይገኙበታል።

ከሁለት አመት በፊት ኢትዮጵያ እንደ ዘንድሮው ሁሉ በ17ኛ ደረጃ ላይ ትገኝ የነበረ ሲሆን፣ አምና ግን ደረጃዋን በማሻሻል ወደ 20ኛ ዝቅ ብላ ነበር። በዚህ አመትም በአገሪቱ ውስጥ የሚፈጸመው የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መክፋቱን መረጃው ያሳያል። ከአንድ እስከ 20 ባለው ዝርዝር ውስጥ የሚገኙ አገሮች የመፈራረስ አደጋ ያንዣበበባቸው አገሮች ናቸው። ሶማሊያ አሁንም በቀደማኒነት ትመራለች። ወያኔና ግብረአበሮቹ በሽብርተኛነትና በመልካም አስተዳደር ጉድለት ሁሌም የሚወነጅሏት ኤርትራ አሁን ይፋ በሆነው መረጃ ከኢትዮጵያ በተሻለ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ መረጃው ይፋ አድርጎአል።

አዲሱ መረጃ የኢትዮጵያን ማህበራዊ እና ኢኮሚያዊ ችግሮች እያሻሻልኩ፣ አገሪቱን ወደ መካከለኛ ገቢ ለማሳደግ ግስጋሴ ላይ ነኝ ለሚለው የመለስ አገዛዝ የሚያቀርበውን ተደጋጋሚ ፕሮፓጋንዳ የሚቃረን ነው። የኢትዮጵያ ህልውና ከጊዜ ወደ ጊዜ አደጋ ውስጥ መውደቁን አለመቃቱ የግጭቶች አስወጋጅ ድርጅት ባወጣው ሪፖርት መግለጹ ይታወሳል። በቅርቡ አሜሪካ መንግስት ስቴት ዲፓርትመንትም ለኢትዮጵያ ህልውና አደገኛ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችና እና የጎሳ ግጭቶችን በዝርዝር አቅርቧል።

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የወያኔው አገዛዝ በእስር ቤት ባጎራቸው ንጹሃን ዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለው ሰቆቃ እንዲቆም አለም አቀፉ ማህበረሰብ አስፈላጊውን ተጽዕኖ እንዲያደርግ አንድነት ባወጣው መግለጫ ጠየቀ

መለው የኢትዮጵያ ህዝብ መንግስት የህሊና እስረኛ ባደረጋቸው ዜጎች ህይወትና ደህንነትን ላይ የሚወስደውን ሃላፊነት የጎደለው እርምጃ በትኩረት በመከታተል አስፈላጊውን ጫና እንዲያሳድር የሃይማኖት መሪዎች እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ተሚጋቾችም የእነዚህን ውድ ኢትዮጵያዊያን ህይወት ለመታደግ የተለየ ጥረት እንዲያደርጉ፣ አለም አቀፉ ማህበረሰብ በበኩሉ ይህንን ሁኔታ በአንክሮ በመከታተልና የገዥዎቻችን ባህሪ ይበልጥ በመረዳት ከሰላማዊ ታጋዮች ጎን እንዲቆም አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሰሞኑን ባወጥው መግለጫ ጥሪ አስተላለፈ።

አንድነት በቅርቡ ከእሥር ቤቱ የወጣን አንድ ሠነድ ጠቅሶ በመግለጫው እንዳለው በቃሊቲ እስር ቤት የታሰሩ የህሊና እስረኞች በርካታ በደሎች እየተፈጸሙባቸው ነው:: የፍርድ ቤት ጉዳያቸው ሆን ተብሎ ያለ አግባብ ይጓተታል:: በእሥር ቤቱ ፖሊሶችና ኃላፊዎች ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ ዘለፋዎችና አሰቃቂ ድብደባዎች ይፈጸሙባቸዋል:: የፖለቲካ እሥረኞች ሆነው ሳለ፤ ሞራላቸውን ለመንካት ሲባል እጆቻቸው በካቴና አሥረው ለሕዝብ ያሳይዋቸዋል:: ከሕግ ውጪ የህሊና እሥረኞች ከደረቅ ወንጀል እሥረኞች ጋር አብረው እንዲታሰሩና ሆን ተብሎ እዲደበደቡ ይደረጋል። በጓደኞቻቸው፤ በዘመድ ወዳጆቻቸው በሃይማኖትም ሆነ በሕግ አማካሪዎቻቸው እንዲጎበኙ አይፈቀድላቸውም:: ሲታመሙ በቂ ሕክምና በመከልከል እንዲሰቃዩ ይደረጋል። ጋዜጣ እንዳያነቡ ሬዲዮ እንዳይሰሙ ይከለከላሉ:: እንደ ሌሎች እሥረኞች የሙያም ሆነ የቀለም ትምህርት እንዲማሩ አይፈቀድላቸውም:: ብዙ የደከሙባቸውንና ለተለያየ ጉዳይ ያዘጋጁዋቸውን ጽሑፎች ያልአግባብ ይነጠቃሉ:: ሌላም ሌላም።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር በአገራችን የተንሰራፋው የመልካም አስተዳደር ጉድለትና የፍትህ እጦት የአገዛዙን ዕድሜ እያሳጠረ እንደሆነ በርዕሰ አንቀጹ አስጠነቀቀ

"በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በቃል፣ በራዕይ፣ በፖስተር፣ በቢልቦርድ ስለፍትሕና መልካም አስተዳደር ብዙ ቢነገርና ቢለፈፍም በተግባር ግን ፍጹም የለም፤ ሕዝብ ደግሞ መግለጫ በቃ፣ ዕቅድ በቃ፣ ቃለ መጠይቅ በቃ:: የናፈቀን ተግባር ነው:: ፍትሕና መልካም አስተዳደርን እውን የሚያደርግ ተግባር እያለ ነው ሲል አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ከትናንትና በስቲያ እሁድ በታተመው ጋዜጣ ርዕሰ አንቀጽ ገለጸ።

ሪፖርተር ህዝቡን እያሰመረረ ነው ባለው የፍትህ ጉድለትና የመልካም አስተዳደር እጦት ምክንያት ጉበኝነትና ሙስና እጅግ መስፋፋቱን የዘረኛው ወያኔ ቁንጮ የሆነው መለስ ዜናዊ ጭምር የግል ብቻ ሳይሆኑ የመንግሥት ሌቦችም አሉ በማለት በአደባባይ መለፈፉን ገለጾ ሆኖም ግን አሉ በተባሉ የመንግሥት ሌቦች ላይ አንዳችም ዕርምጃ ሲወሰድ ግን አይታይም ሲል አክሏል።

ራዕይና ዓላማ ቀልድ ሆነዋል:: ሐሳብ መስጫ ሳጥን ፌዝ ነው ያለው ጋዜጣው ዜጎች አቤት ማለት መብታቸው መሆኑና ኃላፊዎች የሕዝብን ቅሬታ ማስተናገድ ግዴታቸው እንደሆነ ተዘንግቷል::በመሆኑም ዜጎች ይሸማቀቃሉ:: ሹመኞች ይቀልዳሉ:: እንዲያውም የመንግሥት አካላትን የሚያንቀሳቅሱና የሚያሽከረክሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ የግል ማፍያዎች መኖራቸው ይበልጥ አስደንጋጭ ነው - በመንግስት ላይ ሌላ መንግስት ያለ አስመስሎአል በማለት አብራርቷል።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በችግር አረንቋ ውስጥ እየዳከረች ያለች ሀገር መሆኗን ያመላከተው ሪፖርተር በዋነኛነት የኑሮ ውድነት ጣራ መንካቱን በማንሳት የፍትህና የመልካም አስተዳደር እጦት ችግሮችም በቃላት ሊገለጹ ከሚችሉ በላይ መሆናቸውን ገልጿል። እንደ ጋዜጣው የፍትሕ አካላት ራሳቸው ፍትሕ ያጡ ናቸው:: በቴሌፎንና በአካል ያልሆነ ትዕዛዝና ጫና ይደርስባቸዋል:: ነፃ ሆነው መሥራት የሚቸገሩበት ሁኔታ አለ:: ፍትሕ ያላገኘ ዳኛ ደግሞ ፍትሕ መስጠት አይችልም::

ከዚህም ሌላ ስርዓቱ በሙስና የተጨማለቀ ሆኗል።ገንዘብ በህገ መንግስቱና በማስፈጸሚያ ህጎቹ ላይ የበላይነት የያዘበት የፍትህ ስርዓት ውስጥ ነው ሀገሪቱ ያለችው፤የአቅም ማነስም ሌላው የፍትህ ስርዓቱ ችግር ነው።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመለስ ስካይፐ መከልከል እንድምታ

መለስ ዜናዊ ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ ለመግዛት ያለውን ብርቱ ፍላጎት ገላጭ ከሆኑ ነገሮች አንዱ በኢንተርኔት አማካይነት በድምጽና በምስል መገናኘት በሚያስችሉ መሣሪያዎች መጠቀምን ህገወጥ ለማድረግ ያወጣው አዋጅ ነው። ይህ ሰሞኑን ዓለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙሃን በስፋት የዘገቡት እና ሰሚውን ሁሉ "ጉድ" ያሰኘ እርምጃ ነው።

በ19ኛው ክፍለዘመን የቴሌኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንደተፈለሰፈ የወቅቱ ንጉሥ አፄ ሚኒሊክ አገራችንን የትሩፋቱ ቀዳሚ ተቋዳሽ እንድትሆን አድርገዋታል። ይሁን እንጂ ያኔ ቀዳሚ የነበረችው አገራችን ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስርጭት የዓለም ጭራ ሁናለች። ዘረኛው መለስ ዜናዊ ግን በዚህ አልረካም፤ ከዚህም ወደባሰ ጨለማ ሊጎትታት ቆርጦ ተነስቷል። ለዚህም ህግ አውጥቷል።

እንደሚታወቀው ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ሃብታም ሃገራት ብቻ ሳይሆኑ ድሃ ሃገራትም ጭምር በቀላሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ የቻሉበት የቴክኖሎጂ ዘርፍ ነው። ዛሬ በብዙ ድሃ አገራት የኮሚኒኬሽን ወጪ እጅግ ዝቅተኛ አሊያም ነፃ ነው። በዚህ ርካሽና ቀልጣፋ የኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም አገሮች የርቀት ትምህርት፣ የርቀት ህክምና፣ የርቀት ንግድ ... ወዘተ እያስፋፉ ነው። ሰዎች በየቤታቸው ወይም በየቢሮዓቸው ውስጥ ሆነው በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ካሉ አጋሮቻቸው ጋር ስብሰባዎችን ማካሄድና ሥራቸውን ማቀላጠፍ ችለዋል። ይህ የቴክኖኖጂ ዘርፍ ለበርካታ ድሃ አገሮች የእድገትና ብልጽግና ምሰሶ ሆኗል።

ኢትዮጵያ ግን ለዚህ አልታደለችም። ማናቸውንም ነገሮች ከራሱ ስልጣን መረጋጋት አንፃር ብቻ የሚመዝነው የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አገዛዝ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን የሚጠቀመው "ለአገዛዜ ያሰጉኛል" የሚላቸውን የራድዮና የቴሌቪዥን ስርጭቶችን ለማፈን፤ ለፍትህና ለነፃነት የሚታገሉ ኢትዮጵያዊያንን ለመሰለል እና የራሱን ውሸቶች ለማሰራጨት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተራ የሆነ የኤሌክትሮኒክስ ፓስታ (ኢሜል) አገልግሎት እንኳን በወጉ እንዳያገኝ ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኩባንያ (ኢትዮቴሌኮም) ሕዝብን ከማገናኘት ሕዝብን ለመሰለል የሚያጠፋዉ ግዜ ይበልጣል። ኢትዮቴሌኮም በዓለም እጅግ ኋላቀርና ደካማ አገግሎት እየሰጠ እሱንም ለስለላ ተግባር የሚያውል መሆኑ የሚያሳዝን ነው ተብሎ የሚታለፍ ጉዳይ አይደለም። ኢትዮቴሌኮም የደንበኞቹን ምሥጢር አሳልፎ የሚሰጥ አንዳችም የዘመናዊ ኮርፖሬሽን ባህርይ የሌለው አሳፋሪ ድርጅት ነው። ኢትዮቴሌኮም እንደማንኛውም የአገዛዙ የመጨቆኛ መሣሪያ መወገዝ ይኖርበታል።

በተለይም ሰሞኑን "በቴሌኮም አገልግሎት ላይ የሚደረገውን ማጭበርበር ለመቆጣጠር" በሚል ሽፋን የወጣው አፋኝ አዋጅ የዜጎች የመናገር፣ የማወቅ፣ የመወያየት መብቶችን የሚገፍ፤ የግለሰብ ሚስጢሮችን የሚደፍር እና የዜጎችና የአገራችን ሁለንተናዊ እድገት የሚያቀጭጭ ነው። ይህ አዋጅ ህገ-አልባነትን ህጋዊ ከሚያደርገውና መለስ "የፀረ-ሽብር ህግ" ብሎ ከሚጠራው አዋጅ የማይተናነስ ነው።

በዚህ አፋኝ አዋጅ መሰረት "የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር" ከሚባለው የስለላ ተቋም ፈቃድ ውጪ ማንኛውንም አይነት የቴሌኮሚኒኬሽን መሣሪያ ማምረት፣ መገጣጠም፣ ከውጭ ሃገር ማስመጣት፣ መሸጥ እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና እስከ 150ሺህ ብር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ያስቀጣል።

ከጥቂት ወራት በፊት ራሱ ኢትዮቴሌኮም ስካይፐ፣ ፍሪኮል፣ ጉጉል ቶክ እና የመሳሰሉትን በመጠቀም እንዴት በቀላል ወጪ በምስልና በድምጽ መገናኘት እንደሚቻል በድረገጹ ትምህርታዊ ገለፃ ይሰጥ ነበር። በአዲሱ አዋጅ ግን ራሱ ሲያስተምራቸው የነበሩ አገልግሎቶችን መጠቀም እስከ 15 ዓመት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደርገዋል።

ይህ ምን ማለት ነው? እንዴት ነው አፍሪቃን ጨምሮ በመላው ዓለም ሕዝብ በነፃ የሚጠቀምበትን የስካይፐ ቴክኖሎጂ መጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ በ15 ዓመት እስር የሚያስቀጣው?

በስካይፐ እና በመሳሰሉት የኢንተርኔት ግኑኝነት ምክንያት የኢትዮቴሌኮም ገቢ መቀነሱ ለአዋጁ መውጣት ምክንያታቸው እንደሆነ የመለስ ዜናዊ ባለሟሎች ነግረውናል። ይህ ምክንያት ግን ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። የቴክኖሎጂ ለውጥ የመጣው በመላው ዓለም ላይ እንጂ በኢትዮቴሌኮም ላይ ብቻ አይደለም። "ገቢ ይቀንስብኛል" በሚል ሰበብ የተሻሻለ ቴክኖሎጂን ማፈን ትውልድን መበደል ነው። ይህ ደግሞ ወንጀል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝብ ስካይፐ ሲከለከል በመደበኛ ቴሌፎን ይጠቀማል ብሎ ማሰብ አላዋቂነት ነው። የዋጋ መጨመር የፍላጎት መቀነስን ማስከተሉ የማይቀር ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ አዋጁ "መናገር ክልክል ነው" ከሚል ጭፍን እገዳ አይለይም። የመናገር መብት ደግሞ መሠረታዊ ከሆኑ የሰው ልጆች መብቶች ውስጥ ዋነኛው ነው።

የአዋጁ ሁለተኛ ምክንያት የተባለው፣ ዋነውና ብቸኛው የአዋጁ ምክንያት ነው። ይህም "የደህነት ስጋት" የተባለው ነው። እውነት ነው ነፃ የሕዝብ ከሕዝብ ግኑኝነት የመለስን አገዛዝ ስጋት ላይ ይጥላል። በዚህም ምክንያት መለስ ዜናዊ የማይቆጣጠረው መገናኛ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖር አይፈቀድም። ስካይፐ ለቁጥጥር አያመችም። እናም መለስ "ስካይፐ መጥፋት አለበት" ብሎ ወስኗል ማለት ነው። ሆኖም ግን ስካይፐን መዝጋትም ሆነ ማፈን አስቸጋሪ በመሆኑ ለመለስ ዜናዊ የተሻለው አማራጭ ሆኖ የተገኘው የቅጣቱን መጠን በማብዛት ተጠቃሚን ማስፈራራት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በዚህ ማስፈራሪያ የሚሸበር አይደለም። ፈጠራን ማፈን የሚሆን ነገር አይደለም። የቱኒዚያው ቤን አሊ፣ የግብጹ ሙባረክ፣ የሊቢያው ጋዳፊ እና የየመኑ አሊ አብዳላ ሳልህም ሞክረውት አልተሳካላቸውም። በቴክኖሎጂ ላይ ለሚደረግ አፈና የቴክኖሎጂ መፍትሄ አለው። እንዲያዉም አዋጁ የስካይፐ ተጠቃሚ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲጨምር ያደርጋል ብለን እናምናለን። እናም መለስ ስካይፐን በማፈን የሥልጣን እድሜውን ለማርዘም ማሰቡ ስህተት ነው። ይልቁንም አፈናው የመለስ ዜናዊ አገዛዝን ይበልጥ በማሳጠር ረገድ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል ብለን እናምናለን። ስካይፐን መከልከል የነፃነት ቀንን ያቀርበው እንደሆን እንጂ አያርቀውም።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ዘርፍ የሚያደርገውን አፈና አጥብቆ ይቃወማል። መለስ ካልተወገደ በስተቀር እንዲህ ዓይነቱ ለማመን የሚቸግሩ ህገ-ወጥ እርጃዎች ይኖራሉ። ለንቅናቄዓችን መፍትሄው ግልጽ ነው። ይህም መለስ ዜናዊ እና አገዛዙን ማስወገድ ነው። እኛ ለዚህ ተነስተናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኛ ጋር ነውና ነፃነታችንን እንቀዳጃለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

## የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ባለሥልጣኖች ከህዝብ የዘረፉትንና በሙስና ያከማቹትን ገንዘብ ከአገር በማሸሽ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ያካሄዱት ከመለስ ዜናዊ ሚስት አዘብ መስፍን ጋር ተመሳጥሮ በመሆኑ ብቻቸውን ሊወነጀሉ እንደማይገባ ተከራክረው እንደነበርና መዘገቡ አይዘነጋም። የሙስና እሜቤት የሚል ቅጽል ስም የወጣላት የአዜብ መስፍን ስም በመነሳቱ ምክንያት በደቡብና በጋምቤላ ክልሎች ተደርጎ የነበረው ግምገማ ውጤት እንደተድበሰበሰ ሲታወቅ ያንን የተመለከቱና ልብ ልብ የተሰማቸው ሹመኞች የሚያካሂዱትን ዘረፋ አጠናክረው ቀጥለውበታል ተብሎአል።

መለስ ዜናዊ አሜሪካን አገር ላይ አንገቱን የሚያስደፋና ፍርሃቱን ያጋለጠ ተቃውሞ እንደገጠመው ወሬው በመላው አገሪቱ ውስጥ በሰፊው በመሰራጨቱ ብዙ አባላቱና ደጋፊዎቹ የአገዛዙ ዕድሜ እያጠረ መምጣቱን አመልካች አድርገው እምነት እያጡ መምጣታቸው ይነገራል።

ካለፉት 3 ቀናት ወዲህ የመለስ ዜናዊ ጤንነት እጅግ እያሽቆለቆለ በመሄድ ላይ መሆኑን የሚያሳይ የገረጣና የጠወለገው ሰውነቱ ሚስል በሚዲያ ከቀረበ ወዲህ በውጪ አገር የሚኖሩ ደጋፊዎቹ ዘንድ ድንጋጤ እንደተፈጠረ ዝግጅት ክፍላችን ያሰባሰባቸው የህዝብ አሰታያየት ያረጋግጣል።

## አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር በአገራችን የተንሰራፋው የመልካም አስተዳደር . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

እየታየ ያለው ችግር ግን በፍርድ ቤቶች ብቻ የተገታ አይደለም:: በሁሉም የመንግሥት መሥርያ ቤቶች ከፍተኛ ችግሮች ይታያሉ:: በወረዳና በክፍለ ከተሞች፣ በማዘጋጃ ቤቶች፣ በሚኒስቴር መሥርያ ቤቶች ያፈጠጡ ችግሮች አሉ:: በኤጀንሲ፣ በኮሚሽን፣ በባለሥልጣን መስሪያ ቤቶችም እንዲሁ:: በተቀመጠላቸው ኃላፊነትና ግዴታ ሕዝብን እያገለገሉ አይደሉም::

የብቃት ማነስም በመንግሥት መሥርያ ቤቶች በእጅጉ እየታየ ነው:: መንግሥት ምን አይቶ በምን መዝኖ እዚያ ቦታ ላይ እንዳስቀመጣቸው ግራ የሚያጋባና የሚያሳዝን ነው:: ሕዝብን የሚጎዱትን ያህል መንግሥትንም ይጎዳሉ:: አባልነትና ደጋፊነት መመዘኛ ከሆነም የተሻለ አባልና ደጋፊ አጥተው ነው ወይ? ያሰኛል በማለት የስርዓቱን መበስበስ በቁጭት የገለጸው ሪፖርተር ዛሬ ሕዝብ ጉዳዩን ለማስፈጸም ወደ መንግሥት መሥርያ ቤት ለመሄድ እየተሸማቀቀ ነው:: የሚሰማኝ አገኛለሁ ብሎ አያምንም:: ፍትሐዊ ውሳኔ አገኛለሁ የሚል አስተሳሰቡ ጨለምተኛ ነው:: ካለ ጉቦ ያልቅልኛል የሚል ተስፋም የለውም ብሏል::

በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው አንድ አስተያየት ሰጪ እንዳሉት የህወሃት አባልና በአንድ ወቅት ማስታወቂያ ሚንስቴር የፕሬስ ሃላፊ የነበረው አማረ አረጋዊ በሚያስተዳድረው የሪፖርተር ጋዜጣ ይህንን ሃቅ ለመግለጽ የተገደደው በንቅዘት ብዛት አይኑ እያየ እየተፈረካከሰ ያለውን ፓርቲውን ከሞት ለማዳን አስቦ ቢሆንም ተጨባጭ እውነታዎቹ የሚያሳዩት ግን ስርዓቱ አንድም ቦታ ሳይቀር ፍጹም መበስበሱንና ወደ አይቀሬው ሞቱ እያደረገው ያለው ጉዞ መፋጠን ደጋፊዎቹንና አባላቱን ጣር ውስጥ የከተታቸው መሆኑን ነው።

# በህግ አምላክ ሲባል የማይሰማ መንግስት ዛሬ መወገድ ይገባዋል

እነ መለስ ዜናዊን የመሳሰሉ ዘረኞች የሚክዱት እኛ ግን የምንቀበለው የኢትዮጵያ ታሪክ ብዙና ረዥም ነው። በዚህ የረዥም ዘመን ታሪክ ውስጥ ዜጎቿ ህግን ሠርተው የሠሩትንም ህግ አክብረው የሚኖሩባት ትልቅ አገር ነበረች። ዜጎች ለህግ ያላቸውን ክብር ሲገልጡም "በህግ አምላክ" እየተባባሉ ወንጀልን ይቀንሱ ወይም ይከላከሉ ነበር። በህግ አምላክ የሚል ድምጽ ከተሰማ ሁሉም ባለበት ርግቶ ይቆማል እንጂ ድምጹን ረግጦ መሄድ የጨዋ ልማድ አልነበረም። ህግ እንደዛሬ እንዲህ የበቀልኞች ቂም መወጣጪያ ከመሆኑ በፊት በአገራችን ከፈጣሪ ቀጥሎ ተከብሮ ፍትህን አጽንቶ ቆይቷል።

ዛሬ በአገራችን አለቦታቸው የተነሱ ዘረኛ ቡድኖች የዘረኝነታቸውን ማሡሪያ ለማጥበቅ ህግ ሠርተው ዜጎችን የማጥቂያ መሳሪያ አድርገው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። እነዚህ ዘረኞች የገነቡት "ህገ አራዊት " ዜጎችን ለማጥቂያነት በመዋሉ በኢትዮጵያችን ፍትህ መቀለጃ መሳለቂያ ሁናለች።በኢትዮጵያችን ውስጥ ህግ በመጥፋቱ፤ ፍትህም መቀለጃ መሳለቂያ በመሆኗ አገሪቷ የጨካኝ ነፍሰ ገዳዮች እና የሌቦች መናኸሪያ ሁናለች። አሁን በዚህ ዘመን በአፈሪካ ውስጥ ከሶማሊያ ቀጥሎ ህግ አልባ አገር ኢትዮጵያ ነች። ዜጎች በየመንገዱ ተገድለው የሚጣሉባት፤ መንግስት የምታመልኩትን እኔ ልመርጥላችሁ የሚልባት፤ ገዥው ቡድን ዜጎችን አለ ህግ የሚያስርበት እና የሚያሰቃይበት አገር ኢትዮጵያ ነች።

በህግ አምላክ ሲባል የማይሰማው ነውረኛው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የስልጣን ወንበሩን ከተቆናጠጠ ግዜ ጀምሮ በአገሪቷ ውስጥ ብዙ ዜጎች አልቅሰዋል፤አለአግባብ ታስረዋል፤ ተገድለዋል፤ ከቦታቸው ተፈናቅለዋል። በአገሪቷ ውስጥ ህግ ቂም መወጣጫ በመሆኑ ከአገራቸው በሚሰደዱ ዜጎች ብዛት ኢትዮጵያ ስሟ የሚጠቀስም ሁናለች። የተሰደዱትንም ዜጎች የደረሰባቸውን መከራና ስቃይ፤ በየበረሃው ቀልጠው የቀሩትን፤ የባህር አዞ የተቀራመታቸውን ወገኖቻችንን ባየንና በሰማን ግዜ ውረደትና ሃዘኑ መሸከም ከምንችለው በላይ ሁኖብናል። እንደ ቀድሞ አባቶቻችንና አያቶቻችንም አንገታችንን ቀና አድርገን በሰው መሃል ለመቆም የሚቻለንም አልሆነም። መለስ ዜናዊን ለመሰሉ ነውረኛ ዘረኞች ግን ይሄ ስኬታቸው እና ሰላማቸው ሁኖ በየደረሱበት ሁሉ እዩን እዩን እያሉ ነው። እንዲህ በነውራቸው መከበርን የሚፈልጉ ዘባተሎዎች በአገራችን ላይ መሰልጠናቸው የህግ አላባ አገር ውጤት ነው።

ባንድ ወቅት ህግ አልባ በሆነችው ሶማሌ ጎዳናዎች ላይ የጠይሞቹ የአገራችን ልጆች አስከሬን በገመድ ታስሮ እንደ ሞተ ውሻ ሲጎተት በዓይናችን አይተን አንገታችንን ደፍተን ነበር። ይህስ ከቶ ለምን ሆነ ብለን ብንጠይቅም መልስ የሚሰጠን አላገኘንም። በዚህ ምንነቱ ባልታወቀ ጦርነት ውስጥ ሂደው በየሜዳው የወደቁ ኢትዮጵያዊያን በመታየታቸው አገራችን ተዋረደች እንጂ አልከበረችም። ይሄን የመሰለ ውርደት ለዜጎቻችን ያተረፉት እነመለስ ዜናዊ ይሄንንም አረመኔያዊ ድርጊት በኢትዮጵያ ምድር ላይ ዳግም ፈጸሙትና በዓይናችን አየን በጆሮአችንም ሰማን። የኢትዮጵያዊ አስክሬን በሶማሊያ ጎዳናዎች ላይ ቢጎተት ሶማሊያዊያን ያን ለማድረግ የራሳቸው እውነት ይኖራቸው ይሆናል፤ በገዛ አገራችን ላይ ተገድለው ሬሳቸው በየጎዳና ላይ ስለመጎተቱ የዘረኞቹ ቡድን ምን መልስ ይኖረው ይሆን ? ይሄስ አረመኔያዊ ተግባር ኢትዮጵያን አስተዳድራለሁ ብሎ ራሱን በሾመ ኃይል ተፈጸመ ቢባልስ ማን ያምናል? ብናምንም ባናምንም ግን በጎንደር ክፍለ ሃገር የኢትዮጵያዊያን አስከሬን በመኪና ታስሮ በጎዳና ላይ ተጎትቶ ዜጎች አይተዋል፤ ሰምተዋልም። ህግን የማያውቁ ወሮበላዎች ከሚገለጡበት ብዙ ጭካኔዎች መካከል አንደኛው ይሄው ነው።

ደርግ ***"የገደልኩበትን የቀለሃ ዋጋ ክፍሉኝ"*** ብሏል እያለ የሚከሰው መለስ ዜናዊ ከደርጉ የከፋ ጭካኔ በኢትዮጵያዊያን ላይ እየፈጸመ ይገኛል።መለስ ዜናዊን የመሰለ መርገምት በአገራችን ላይ ተጭኖ ኢትዮጵያዊያኑም ይህን እርግማን ተሸክመን እንኖር ዘንድ አይገባም። መለስ እና ዘረኛና ሌባ ቡድኑን ተሸክሞ መኖር ያተረፈልን ውርደት በቃላት መግለጽ ከምንችለው በላይ ነው።ብዙ ነውሮች፤ በዙ ጭካኔዎች በአገራችን ላይ መፈጸማቸውን ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያውቀዋል። ምንም የተከደነ፤ ምንም የተሰወረ ነገር የለም። ሁሉም ግልጽና የታወቀ ነው። ይሄ ግን መብቃት ይኖርበታል።

ህግ የማይገዛው ይሄ ዘረኛ ቡድን ከሰሞኑ በአዲስ አበባ በተቀደሰው ስፍራ እርኩሰት መፈጸሙን አይናችንን ከፍተን ዓይተናል፤ ጆሮአችንንም አቅንተን ሰምተናል።

በቤተ-መቅደስ ውስጥ ዘልቀው ገብተው ቅዳሴ አስታጉለው ቀሳውስቱንና ምእመናኑን ከቤተክርስትያን በማባረርና ቤተ-መቅደሱን በመበዝበዝ ቤተክርስትያኒቷን አዋርደዋል። ቤተመቅደስ በመደፈሩም ምእመናኑ እሪ ቢሉም ከቄሳሩ ጋር መቆምን የመረጡ የሃያምኖቱ መሪዎች ያሉት ነገር አልተሰማም። እነዚህ ጨካኞች ለወንጀላቸው መሸፈኛም ይሆናቸው ዘንድ የሰላም ደጅ ተብላ በምትጠራው ቤተክርስትያን ግቢ ውስጥ የአንድ ድሃ ፖሊስ ደም አፍሰዋል። የዚህ ምስኪን ፓሊስ ደም "ሁሉን አዋቂ፤ ሁሉን አድራጊ" ተደርጎ በአምላኪዎቹ ዘንድ ለሚታወቀው ጣኦቱ መለስ ዜናዊ እድሜ ማቆያ የቀረበ መስዋእት ነው።እጁን በንጹሃን ደም ታጥቦ መኖርን ልማዱ ያደረገው መለስም መስዋእቱን ተቀብሎ ረክቶና ደስ ብሎት ዛሬን አድሯል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የቆመበትን መሠረት ለይቶ ማየት የተሳነውና መለስ ዜናዊን እንደ አምላኩ የሚያየው ኩማ ደመቀሳም ራሱ መክሮና ዘክሮ መስዋእት አድርጎ ያቀረበውን ወጣት "ገዳይ" ለመያዝ በሚል ሰበብ መንደሩንና ደብሩን እያመሰው ነው። በዚህም ብዙ ወጣቶች ወደ እስር ቤት ተግዘው የመከራ እንጀራን እንዲበሉ፤ የመከራ ጽዋንም እንዲጠጡ እየተደረገ ነው። ህወሃቶች እንዲህ ያለ ነውር ሲፈጸሙ የመጀመሪያቸው አይደለም። ብዙ ነውሮች፤ ብዙ ድፈረቶች በተቀደሱ ስፍራዎች ተፈጽመዋል።የብዙ ንጹሃንንም ደም እንዲሁ በከንቱ አፍሰዋል።

ህግን የሚያከብር፤ ህዝብንም የሚፈራ መንግስት በኢትዮጵያችን ካልመጣ በተቀደሰው ሥፍራ እርኩሰት ሲፈጸም ማየት የማይቀር ነው።ዘረኛ ገዥዎችም ነውራቸውን እንደ ኩራት፤ ጭካኔአቸውንም እንደ ጀግንነት ቆጥረውት ይኖራሉ እንጂ አይለወጡም። ኢትዮጵያዊያን ግን ይህን በመሰለው ነውር ውስጥ ለመኖር ክብራቸውና ታሪካቸው አይፈቅድላቸውም።መለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑን ሊቀመጡበት ከማይገባቸው ወንበር ላይ አውርዶ ዳግም በተቀደሰው ስፍራ እርኩሰት እንዳይፈጸምና አርመኔያዊ ድርጊቶቻቸው እንዲገታ ለማድረግ ህዝቡ ከመቸውም ግዜ በላይ በአንድነት ሊነሳ የሚገባው አሁን ነው።

ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄም በተቀደሰው ሥፍራ ላይ ዳግም እርኩሰት እንዳይፈጸም ለማድረግ የጀመረውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል። ከጀመርነው ትግል የሚያቆመን የለም። መፈንቀል የጀመርነውን ድንጋይ እንፈነቅላለን። እየሄድን ባለንበት መንገድ ትግላችንን እንቀጥላለን። በምንሄድበት መንገድ ሁሉ እውነት ከእኛ ጋር በመሆኗ ታጸናናለች። የነጻነት ጥያቄ ከእኛ ጋር መልስ ስላላት ተስፋ አንቆርጥም።ዴሞክራሲም በእውነትና በፍትህ ላይ ትመሰረታለች።

በመጨረሻም በህግ አምላክ !!! ሲባል የማይሰማው የመለስ ዜናዊ ቡድን እንዲወገድ ትግላችን ተጠናክሮ በተጀመረው መንገድ ተጠናክሮ ይቀጥላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**
**እግዚአብሄር ኢትዮጵያችንን ይባርክ !!!**
**አላሁ አኩበር !!!!**

# የወያኔው አገዛዝ በእስር ቤት ባጎራቸው ንጹሃን ዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለው ሰቆቃ እንዲቆም አለም አቀፉ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

እናም ይህ ሁሉ በደል ያንገሸገሻቸው እሥረኞች ከሰኔ 6 ቀን ጀምረው የረሃብ አድማ እያደረጉ ሲሆን ጥያቄያቸው ምላሽ እስከሚያገኝ ድረስ በረሃብ አድማው እንደሚቀጥሉበት ገልጸዋል፡፡

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት አንዳንዶቹ እስረኞች መድከም ጀምረዋል፡፡ የረሃብ አድማው ከቀጠለ በህሊና እስረኞቹ አካል፤ ብሎም በህይወታቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ይህ አሳሳቢ ጉዳይ ተገቢው ትኩርት ተሰጥቶት፤ በቅድሚያ የህሊና እሥረኞቹ ጤንነት በተገቢው መንገድ እንዲረጋገጥ፤ በመቀጠል የረሃብ አድማው ምክንያት የሆኑት ችግሮቻቸው ተገቢውን መፍትሄ እንዲያገኙ፤ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ እንዲጎበኛቸውና ደህንነታቸውን እንዲያረጋግጥ ጠይቋል- አንድነት በመግለጫው።

ለዚህም መላው የህገራችንን ህዝብና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከጎኑ በመቆም በዚህ መንግስት ላይ ጫና እንዲያሳድሩ ተጣርቷል።

በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው አንድ የፖለቲካ ባለሙያ እንዳሉት በእርግጥ እነኚህን እስረኞ ለመታደግ መረባረብ ተገቢ ነው።ግን በዚህ ዓይነት እስከ መቼ ይዘለቃል?የሚለው ጥያቄ መልስ ይሻል። በዚሁ መንገድ እንቀጥል ካልን ነገም መታሰር ነገም መለመን ሆኖ ሊቀር ነው እጣ ፈንታችን። እናም አዙሪቱን መስበር አለብን ካልን ይህንን አዳዲስ መከራ፣ ሰቆቃና ግፍ አምራች ስርዓት አሁን ለሞቱ እያጣጣረ ባለበት ወቅት በጋራ በመረባረብ ሸኝተን አዲስ፣ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ስርዓት መመሰርት ብቻነው ብቸኛው መፍትሄ ብለዋል።

## ኢትዮጵያ የሚሄድ ማንኛውም ሰው እንደ ስካይፕ ዓይነት የድምጽና የምስል መገናኛ ዘዴዎችን እንዳይገለገል ሳልቫዶር ሮደሪጎዝ የተባሉ ጸሃፊ ሎስአንጀለስ ታይምስ ላይ ባወጡት ጽሁፍ አስጠነቀቁ

በዚሁ ጽሁፋቸው ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ አስበዋል? እንግዲያውስ አንድ ምክር ልለግስዎ፤ እዛች ሀገር ውስጥ በፍጹም ስካይፕ አይጠቀሙ፤ እጠቀማለሁ ካሉ ግን ለሚቀጥሉት 15 ዓመታት ከኢትዮጵያ እደማይመለሱ ይወቁ ብለዋል።

ምክንያቱ ደግሞ አሉ ሮደሪጎዝ የኢትዮጵያ መንግስት በቅርቡ ያወጣው በድምጽና በምስል አገልግሎት የሚሰጡ የኢንተርኔት የመገናኛ ዘዴዎች መጠቀምን ወንጀል የሚያደርገው ህግ ነው።

ይህ ህግ ደግሞ በጉግል ቮይስ፣ በስካይፕና በሌሎችም ተመሳሳይ የመገናኛ ዘዴዎች መጠቀምን ያጠቃልላል። በነዚህ የመገናኛ ዘዴዎች ሲጠቀም የተገኘ ማንኛውም ሰው በ15 ዓመት እስራት ይቀጣል። እናም ጠንቀቅ ይበጃል ሲሉ አብራርተዋል።

በእርግጥ ነባራዊ እውነታውን ስንመለከት ይህ ብዙ የሚያስደንቅ አይደለም ያሉት ሮደሪጎዝ የቢቢሲን ዘገባ ለአብነት አንስተዋል።

እንደ ቢቢሲ ዘገባ የኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ ማህደር የሚያሳየው መንግስት ጋዜጠኞችና ዜጎቹ በመገናኛ ዘዴዎች የሚያደርጉትን ማናቸውንም እንቅስቃሴ ለመቆጣጠርና ለማፈን ቅድመ ምርመራን እንደ ዋነኛ ዘዴ እየተገለገለ መሆኑን ነው። በመሆኑም እንደ መደበኛ ስልክ በቀላሉ ለመጥለፍ የማያመቹትን እንደ ስካይፕ ዓይነት የመገናኛ ዘዴዎችን ቢከለክል ብዙም አይገርምም።

የቀድሞዋ በኢትዮጵያ የቢ.ቢ.ሲ. ዘጋቢ ኤሊዛቤት ብለንት በበኩላቸው ለዚህ ህግ መውጣት ተጨማሪ ምክንያት ያሉትን እንዲህ ገልጸውታል በመንግስት ቁጥጥር ስር ያለው ብቸኛው ቴሌኮሙኒኬሽን ከሚያስከፍለው ከፍተኛ ታሪፍ ጋር ሲነጻጸር የኢንተርኔት ካፌዎች የሚያስከፍሉት ዋጋ በእጅጉ ዝቅ ያለ በመሆኑና ገበያውን በመሻማታቸው እነሱን ከዘርፉ አስወጥቶ ገቢውን በብቸኝነት ለመጠቅለል ያለመም ነው።

ሮደሪጎዝ በማያያዝም የኢንተርኔት አገልግሎት በኢትዮጵያ ውስጥ በመስፋፋትም ሆነ በፍጥነት እጅግ አዝጋሚ ነው። 82 ሚሊዮን ከሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል የዚህ መገናኛ ዘዴ ተጠቃሚዎች 360 ሺህ ወይም 0.4 ከመቶ የሚሆኑት ብቻ ናቸው። በዋና ከተማዋ በአዲስ አበባ እንኳን የተጠቃሚነት እድሉ እጅግ ዝቅተኛ ነው ብለዋል። ኢትዮጵያ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባቷና ጥቅም ላይ ከማዋሏ በፊት ላለመቀበል ከፍተኛ መከላከል እንደምታደርግ የቅርብ ጊዜ ማህደሯ እንደሚያመለክት የጠቀሱት ጸሀፊው አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች የሳተላይት ዲሽ ባለቤት መሆን ከ15 ዓመት በፊት ወንጀል ነበር ዛሬ ግን ይህ የመገናኛ ዘዴ ሀገሪቱን አጥለቅልቋታል ክሬዲት ካርድም እንዲሁ ያሉትን አንስተዋል።

እናም እነኚህ ምሳሌዎች የኢትዮጵያ መንግስት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ላይ ያለውን የሁልጊዜ ጥርጥሬና ሁሉንም ነገር ጎጂም ባይሆን በቁጥጥሩ ስር ለማዋል ያለውን ጽኑ ፍላጎት የሚያሳዩ ናቸው ሲሉ ገልጸዋል። በመጨረሻም ምናልባት የኢትዮጵያ መንግስት በስካይፕና በተመሳሳይ የድምጽና የምስል መገናኛዎች ላይ የያዘውን ይህንን አቋሙን ከ 15 ዓመት በኋላ ይቀይር ይሆናል። ያ ወቅት ደግሞ ይህን የመገናኛ ዘዴ በመጠቀማቸው ወደ ወህኒ የተወረወሩት የመጀመሪያዎቹ የስካይፕ ተጠቃሚ ወንጀለኞች ከሚፈቱበት ጊዜ ጋር ይገጣጠማል በማለት ሳልቫዶዶ ሮደሪጎዝ ጽሁፋቸውን አጠቃለዋል።

ወያኔ በኢንተርነት የጀመረውን አፈና በስካይፒና ጉግል ቶክ በመሳሰሉት ዘመናዊ የመገናኛ አገልግሎቶች ላይ ለመውሰድ የደፈረው ተቃዋሚዎች እነዚህን ዘመናዊ መገናኛዎች በመጠቀም ህዝብ በማንቀሳቀስ ከሥልጣን መንበሬ ይፈነቅሉኛል በሚል ስጋት እንደሆነ አልጀዚራንና ቢቢስን የመሳሰሉ ታላላቅ የአለም የዜና አውታሮች ሳይቀሩ በስፋት እየመዘገቡ ነው።

## በኢትዮጵያ ለስኳር ልማት ሲባል አርብቶ አደሮች መሬታቸውን በግዳጅ እንዲለቁ እየተደረገ ነው ሲል ሂውማን ራይትስ ዎች መግለጫ አወጣ

በቂ ምክክር ሳያደርግ ወይም ተገቢውን የካሣ ክፍያ ሳይፈጽም በመንግስት የሚካሄድ የስኳር ልማትን ለማስፋፋት የኢትዮጵያው አገዛዝ በታችኛው የኦሞ ሸለቆ ነዋሪ የሆኑ አርብቶ አደሮችን በግዳጅ እያፈናቀለ ነው ሲል ሂዩማን ራይትስ ዎች ትናንትን ሰኔ 11 ቀን 2004 ዓም ባወጣው ሪፖርት ገለጸ።

ሪፖርቱ ከዚህ በፊት ያልታተሙ እና የመስኖ መስመሮችን፣ የስኳር ማምረቻ ፋብሪካዎችን እንዲሁም ሌሎች ለንግድ የሚውሉ ሰብሎችን ለማማረት የሚውል 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ሄክታር ጨምሮ በኦሞ ሸለቆ ለማካሄድ የታቀደውን ሰፊ ልማት የሚያሳዩ ካርታዎችን ያካተተ ነው።

ሰማንያ አምስት ገጾች ያሉትና "'ረሃብ ቢመጣ ምን ሊኮን ነው?'፡ በኢትዮጵያ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ተወላጅ ነዋሪዎች ላይ የተፈጸሙ በደሎች" በሚል ርዕስ የወጣው ይኸው ሪፖርት የወያኔ የጸጥታ ሃይሎች ሃይልና ማስፈራራትን በመጠቀም ነዋሪዎቹን ከጥንት ጀምሮ ከኖሩበት መሬት እንዴት እንዲለቁ እንደሚያደርጓቸውና ይህም የነዋሪዎቹን ሁለንተናዊ የኑሮ ሁኔታ ያለ ምንም የካሣ ክፍያና አማራጭ የኑሮ መሠረት በማስቀረት እንዴት አደጋ ላይ እንደጣለው የሚዘረዝር ነው። የወያኔ ባለስልጣናት በልማት ዕቅዱ ላይ ጥያቄ ባነሱ እና ተቃውሞአቸውን በገለጹ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ነዋሪዎች ላይ የዘፈቀደ እስር፣ ድብደባና ሌሎች የሃይል እርምጃዎችን ወስደዋል።

"ኢትዮጵያ በኦሞ ሸለቆ ለማካሄድ ያሰበችው ሰፊ የልማት ዕቅድ በዚያ የሚኖሩ ዜጎችን መብቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ አይመስልም፣" ያሉት በሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ከፍተኛ ተመራማሪ ቤን ራውለንስ፣ "ልማት አቋራጭ መንገድ የለውም፤ በዚያ የሚገኘውን መሬት ለዘመናት የኑሮ መሠረታቸው አድርገው የኖሩ ሕዝቦች ሃሳባቸውን ሊጠየቁና ካሣ ሊከፈላቸው ይገባል።" ብለዋል።

እጅግ በጣም ሩቅ የሆነው እና ሰፊ የባሕል ስብጥር ከሚታይባቸው የምድራችን አካባቢዎች መካከል አንዱ የሆነው የታችኛው የኦሞ ሸለቆ ቁጥራቸው 200,000 የሚደርስ በከፊል ግብርና እና ከብት ርቢ የሚተዳደሩና የራሳቸው መለያ ባሕሪያት ያሏቸው ስምንት ማህበረሰቦች የሚኖሩበት ሲሆን እነዚህ ሕዝቦች ዘመን መቆጠር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአካባቢው የኖሩ ናቸው። የኑሮ ዘይቤአቸውና ማንነታቸው ከመሬት እና ለኦሞ ወንዝ ካላቸው ቅርበት ጋር የተቆራኘ ነው። የኦሞ ሸለቆ በኢትዮጵያ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ከኬንያ ድንበር አቅራቢያ የሚገኝ ሲሆን በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የማህበራዊና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የዓለም ቅርስ ተብሎ እ.ኤ.አ በ1980 ተሰይሟል።

በኦሞ ሸለቆ ለማምጣት የታቀደው ከፍተኛ ለውጥ በኦሞ ወንዝ ላይ ከሚገነባውና በከፍታው በአፍሪካ ተወዳዳሪ ከሌለው አወዛጋቢው የጊቤ ሦስት የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ጋር የተያያዘ ነው። በወንዙ የታችኛው ክፍል የሚካሄደው የስኳር ልማት በመስኖ የሚለማ ነው። በጊቤ ግድብ ፕሮጀክት ላይ የተካሄዱ አንዳንድ ነፃ ግምገማዎች ያሉ ቢሆንም በኦሞ ሸለቆ የሚካሄደው የስኳር ልማት እና ሌሎች ለንግድ የሚውሉ ሰብሎች ግብርና እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን አካባቢያዊና ባሕላዊ ተጽዕኖ አስመልክቶ የተካሄደ አንድም ግምገማ የኢትዮጵያ መንግስት እስከዛሬ ይፋ አላደረገም።

ሂዩማን ራይትስ ዎች በሰኔ 2003 ዓ.ም. ከ35 በላይ የአካባቢው ነዋሪዎችና ከ 10 የእርዳታ ሰጪ ሀገራት ተወካዮች ጋር ቃለ መጠይቅ ያደረገ ሲሆን ከዚያ ጊዜ በኋላም ቢያንስ 30 ሌሎች እማኞችን አነጋግሮአል። ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን በጎበኘበት ወቅት ነዋሪዎችን ለማስፈራራትና ከስኳር ልማቱ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ተቃውሞዎችን ለማፈን የጦር ሠራዊት አባላት በመንደሮቹ በየጊዜው ቅኝት ያደርጉ ነበር። ወታደሮቹም (የመንደርተኞቹን) ከብቶች ይሰርቃሉ ወይም ይገድላሉ።

"ምን ልበላ ነው?" ይላሉ የሙርሲ ብሔረሰብ አባል የሆኑ አንድ ሰው ለሂዩማን ራይትስ ዎች ሲናገሩ። "ከብቶቼን በሙሉ ወስጄ እንድሸጥና አንድ ብቻ ከቤቴ እንዳስቀር ነገሩኝ። አንዱን ከብት ምን ላደርገው ነው? እኔ ሙርሲ ነኝ። ረሃብ ቢመጣ የላም አንገት ወግቼ ደም እጠጣለሁ። ከብቶቼን ሁሉ ለገንዘብ ከሸጥናቸው እንዴት ነው የምንበላው?"

ሂዩማን ራይትስ ዎች አካባቢውን ከጎበኘ በኋላ ያሰባሰባቸው ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት የክልሉ ባለስልጣናት እና የጸጥታ ሃይሎች ባላፈው ዓመት የስኳር ልማቱን ለማካሄድ በሚከለለው ቦታ እያረሱ ይኖሩ ከነበሩ የአካባቢው ተወላጆች መሬት በሃይል ነጥቀው ወስደዋል። ነዋሪዎች በሃይል መፈናቀላቸውን እና የመሬት ምንጣሮ መካሄዱን የሚያመላከቱ ሪፖርቶችም እየበረከቱ መጥተዋል።

ወያኔ በአፋር ክልል በተመሳሳይ ሁኔታ ዜጎችን በሃይል ከቄያቸው በማፈናቀሉ በተነሳው ግጭት በአካባቢው ከፍተኛ ውጥረት እንደ ሰፈነ በሰሜን ጎንደር የዋልድባ ይዞታንም እንዲሁ ለስኳር ልማት በሚል ለመውሰድ ውዝግብ ውስጥ እዳለ በተደጋጋ ሚ መዘገባችን ይታወሳል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፦ በ 358 MB, በ 837 kHz

አ<u>ጭር ሞገድ</u>፦ በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችንን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>፦ ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org